STAY SAFE MN



# ልጅዎን ከ COVID-19 ይከላከሉ

የልጀዎን ደህንነት እና ጤና ለመጠበቅ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ይፈልጋሉ። ልጅዎን ማስከተብ አንዱ ልጅዎን ከ COVID-19 እንዲከላከሉ ከሚረዱበት አንዱ ተጨማሪ መንገድ ነው። አሁን የ COVID-19 ክትባት አሁን የሚመከረው 6 ወር እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ህጻናት ነው። ልጅዎን ማስከተብ በትምህርት ቤት፣ በህጻናት እንክብካቤ፣ እና በሌሎች ተግባራት ላይ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ይረዳቸዋል።

- የ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝ ናቸው። የክትባት ደህንነት በጣም አስፈላጊ ነው። ክትባቶቹ ለህጻናት እና ለታዳጊዎች እንዲሰጡ ከመመከራቸው በፊት በጥንቃቄ የተጠኑ እና አስተማማኝ መሆናቸው ታይቷል።
- ህጻናት በ COVID-19 በጣም ሊታመሙ ይችላሉ። ክትባቶች ህጻናትን በ COVID-19 በጣም ከመታመም እና ሆስፒታል ከመሄድ ለመጠበቅ ይረዳል።
- ከክትባት በኋላ ልጅዎ አንዳንድ የጎኞሽ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊያጋጥሟቸዉሙት ይችላሉል፣ ይህም እነኝም ሰውነታቸው ከቫይረስ መከላከያ እየገነባ መሆኑን የሚያሳዩ መደበኛ ምልክቶች ናቸው። የጎንዮሽ ጉዳቶች ባይኖራቸውም ምንም ችግር የለዉም። በእውነቱ፣ ውሂብ እንደሚያሳየው ከትልልቅ ልጆች/አዋቂዎች ጋር ሲነጻጻር ከ5-11 አመት ባሉ የጎኞሽ ጉዳቶች ብዙም ያልተለመዱ ናቸው።
- ምንም እንኳን በCOVID-19 አስቀድሞ ቢያዙም ልጅዎን ማስከተብ አስፈላጊ ነው ምክኒያቱም ክትባቱ ተጨማሪ መከላከያ ይሰጣል።
- የCOVID-19 ክትባቶች ነጻ ናቸው፣ እናም ለመከተብ የመድህን ዋስትና እንዲኖርዎ አይጠበቅም።
- የCOVID-19 ክትባት መሃንነት አያስከትልም።

## ልጅዎን እንዴት ያስከትባሉ እንደምያስከትቡ

- ስለ ቀጠሮዎች የሕፃናት ሐኪምዎን ወይም የቤተሰብ ሕክምና ክሊኒክን ያነጋግሩ።
- አቅራቢዎችን ወይም በአቅራቢያዎ ያሉ መድሃኒት ቤቶችን ለመፈለግና ለማግኘት mn.gov/vaxforkids ይጎብኙ፣ ፦
  - ◊ የህጻናት እና ቤተሰብ የህክምና ክሊኒኮች፣ ቅድመ እክብካቤ አቅራቢዎች፣ በፈደራል ብቁ የሆኑ የጤና ማዕከሎች፣ የሃገር ውስጥ የጤና ድርጅቶች፣ የጎሳ የጤና ድርጅቶች፣ የክልል ማህበረሰብ ቦታዎች እና ክሊኒኮች፣ እና የህንዳዊ የጤና አገልግሎት ቦታዎች።
- በትምህርት ቤት ወይም በሌላ በአካባቢዎ ባሉ ሌሎች የማህበረሰብ ቦታዎች እየተሰጡ ያሉ የክትባት ክሊኒኮችን ይከታተሉ።

## የሚገኙ ክትባቶች

ሁለት የ COVID-19 ክትባቶች አሉ፦ Pfizer እና Moderna። CDC አንዳቸውን ክትባቶች ከሌላው በላይ አበላሊጦ አይመክርም። እያንዳንዱ ክትባት ትንንሽ ህጻናትን በ COVID-19 በጣም እንዳይታመሙ ለመከላከል ይረዳል። ሁሉም የክትባት ቦታዎች እያንዳንዱን ክትባት ላይኖራቸዎረው ይችላል። ዋናው አስፈላጊ ነገር ልጅዎን የሚያስከትቡበትን እድል አለማስመለጥ ነው።



# የ COVID-19 ዶዞች እና በክትባት መካከል ያለው ጊዜ

- ልጅዎ የሚወስደው ክትባት እና የዶዞች ቁጥር እንደየ እድሜያቸው ይወሰናል።
- ከ 6 ወር እስከ 11 አመት ላሉ የህጻናት ክትባቶች ከትልልቅ ህጻናት እና ከአዋቂዎች ክትባቶች ያነሱ የክትባት ዶዝ ያላቸው ናቸው። የክትባት ዶዝ መጠን በልጁ እድሜ የሚወሰን ነው፣ በመጠናቸው ወይም በክብደታቸው አይደለም።
- ህጻናት በመጀመርያ የክትባት ክትትላቸው ለሁሉም ዶዞች ተመሳሳይ የክትባት አይነት መውሰድ አለባቸው። የመጀመሪያ ክትባት ዙር አንድ ሰው የሚያስፈልገውን የአንድ ክትባት የመነሻ ዶዞች ቁጥር ያመለክታል። የማጠናከሪያ ክትባቶችን አያካትትም።
- የለበለጠ ለመከላከል ሁሉንምን የሚመከሩ የክትባት ዶዞች ማግኘት አስፈላጊ ነው። የ Pfizer ክትባት የወሰዱ 5 አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ህጻናት ማጠናከሪያ ዶዝ ማግኘት አለባቸው። የ Moderna ክትባት የወሰዱ ህጻናት በዚህ ጊዜ ማጠናከሪያ እንዲያገኙ አይመከርም።

**Pfizer**
(6 ወር-4 አመት እድሜ)

ዶዝ 1 (የመጀመሪያ) → ከ 3-8 ሳምንታት ውስጥ → ዶዝ 2 (የመጀመሪያ) → ቢያንስ በ 8 ሳምንታት ውስጥ → ዶዝ 3 (የመጀመሪያ)

**Pfizer**
(ከ 5-17 አመት እድሜ)

ዶዝ 1 (የመጀመሪያ) → ከ 3-8 ሳምንታት ውስጥ → ዶዝ 2 (የመጀመሪያ) → ቢያንስ በ 5 ወራት ውስጥ → ዶዝ 3 (አጋዥ)

**Moderna**
(ከ 6 ወር-17 አመትእድሜ)

ዶዝ 1 (የመጀመሪያ) → ከ 4-8 ሳምንታት ውስጥ → ዶዝ 2 (የመጀመሪያ)

የልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎት እና የመጀመሪያውን ዶዝ በሚያገኙበት ጊዜ የሚመከረውን ሁሉንም ዶዞች እቅድ በማዘጋጀት ሊያግዝዎት ይችላል።

ደካማ በሽታ የመከላከል ስርዐት(በሽታ የመከላከል ስርዐት ምላሽ ማደግ አለመቻል) ላላቸው ህጻናት የተለየ ምክሮች ይኖራቸዋል። ወላጆች እና ሞግዚቶች ከልጃቸው የጤና አቅራቢ ጋር መነጋገር አለባቸው።

በክትባት ዶዞች ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ በክትባት አይነት እና እድሜ ላይ ተመስርተው ለሚመከሩ የCOVID-19 ክትባቶች CDC፦ በ-A-Glance የ COVID-19 ክትባት መርሃግብሮች የሚለውን ይገምግሙ።

